# ሦስቱ ቁራዎች

ገለታው ከማር ቤት

ይጮኃሉ፤ ዛሬም እንደ ትናንቱ ያላዝናሉ፤ በየሜዳው፣ በየበረሃው ያንቧርቃሉ - እንዲያው ሰሚ ካገኙ። አለመታደል ሆኖ ግን ልቦናውን ከፍቶ የሚሰማቸው፣ ቀልቡን ሰጥቶ የሚያዳምጣቸው፣ እህሳ ብሎ ጆሮውን የሚያውሳቸው ያገኙ አይመስሉም። እንዲያም ሆኖ ግን እንዳለፉቱ ሁሉ ዛሬም ይጮኃሉ - የቁራ ጩኸት። የዛሬው ጩኸታቸው ከባለፉት ጊዜያት የይዘት ማሻሻያ ይዞ ቀርቧል። የፖለቲካ አቋምን አሊያም የፖለቲካ ፓርቲ ፕሮግራም ልዩነትን መነሻ አላደረጉም።

ይኼ የፖለቲካ መስመር ለአገራችን አይበጅም፤ ይኼኛው ደግሞ ከዛሬይቱ ኢትዮጵያ ነባራዊ ሁኔታ ጋር አይጣጣምም ብሎ ለመሞገት አልፈቀዱም። ግና ጩኸታቸው ዛሬም ላይ በትዝብት ይደመጣል - የሦስቱ ቁራዎች ጩኸት። ስለ ቁራዎቹ ባዶ ጩኸት ወደ ኋላ ይቆየኝና የጽሁፌ ሌላኛው መነሻ ወደሆነኝ ጉዳይ ላምራ ።

ባለፈው ዓመት አጋማሽ ላይ ነገሩ እንዲህ ሆነ። የእንግሊዝ የዜና ማሰራጫ ኮርፖሬሽን /ቢቢሲ/ ኢትዮጵያን አስመልክቶ አንድ ዘገባ በራዲዮ፣ በቴሌቪዥንና በድረ ገፁም ጭምር አሰራጭቶ ነበር።

እስቲ የዘገባውን ዐቢይ ጉዳይ መለስ ብለን እናስታውስ። ቢቢሲ በዚሁ ዘገባው «ህዝባዊ ወያኔ ሓርነት ትግራይ /ህወሓት/ በ1977ቱ ድርቅ ከለጋሾች የተሰበሰበን ከፍተኛ ገንዘብ ለጦር መሣሪያ መሸመቻ አውሎ ነበር» የሚል ነው።

ከሩብ ምዕተ ዓመታት በፊት በድርቅ ለተጎዱ ኢትዮጵያውያን መርጃ እንዲውል የተለገሰው ገንዘብ ለጦር መሣሪያ ግዥ ውሏል ብሎ ቢቢሲ ዘገባውን ያቀረበበት ወቅት የራሱ የሆነ ዓላማና ግብ እንደነበረው ለውድ አንባቢዎቼ ማስታወስን ፈቀድሁ።

ቢቢሲ ይህን መሰል ዘገባውን ለማቅረብ የመረጠበት ጊዜ የኢትዮጵያ ህዝብ አራተኛውን አገራዊ ምርጫ ሊያካሂድ የወር እድሜ በቀረበት ወቅት እንደነበር ልብ ይሏል?

ምናልባትም ያኔ ምርጫው በሠላማዊ ሁኔታ እንዲጠናቀቅ ህዝባዊ መነሳሳት በመታየቱ አጠቃላይ ሂደቱን የማኮሰስ ብሎም የማጨለም ዓላማን ለያዙ ቡድኖች ቢቢሲ በገፀ በረከትነት ያቀረበው ስጦታ እንደነበር የብዙዎች ግምት ሆኖ አልፏል።

ገና ከመነሻው አንስቶ እርዳታው እስከሚከፋፈልበት ሥፍራ ድረስ በአካል እየተገኘና ሂደቱን እየተከታተለ ስለሁኔታው ጤናማ አካሄድ እማኝ ሆኖ የቀረበው የሮክ ሙዚቃ አቀንቃኙ ሰር ቦብ ጌልዶፍ ስለወሬው ሐሰተኛነት ደጋግሞ ቢያስረዳም ሰሚ ጆሮ አላገኘም። በወቅቱ «ባንድ ኤይድ»ን ያስተባብር ለነበረው ቦብ ጌልዶፍ የወሬው ባለቤት ቢቢቢ የሰጠው ምላሽ አለ ከተባለም ዝምታን መምረጥ ነው።

የሆነ ሆኖ ቢቢሲ ሐሰተኛ ዘገባውን በመላው ዓለም ካሰራጨ ከመንፈቅ ዓመት ቆይታ በኋላ «የተሳስቻለሁና ይቅርታ እጠይቃለሁ» ማስተባበያውን አቀረበ።

ዘገባው ሐሰተኛና የተዛባ ስለመሆኑ ከእውነታው ላይ ለመድረስ ምነዋ ይህን ያህል ወራት ያስፈልገው ኖሯል? የዚያን ጊዜ ጥያቄዬ ነበር።

እንዲህ ያለ ቅጥፈት የተሞላበት ዘገባን ማሰራጨት የጋዜጠኝነትን ሙያ «ከእኛ በላይ ላሳር» ብሎ ከሚመፃደቅ ዓለም ዓቀፍ መገናኛ ብዙኋን የሚጠበቅ መስሎ አልተሰማኝም። እንዲህ ያለ ተራ ስህተት በቢቢሲ ደረጃ ባለ ጎምቱ የሚዲያ ተቋም ይፈፀማል ተብሎም አይታሰብም - ሌላ ተንኮል ከሌለ በቀር። ይኼን በዚሁ ላብቃ።

አሁን በዚህ ሰሞን ደግሞ ይኸው የእንግሊዝ የዜና ማሰራጫ ኮርፖሬሽን /ቢቢሲ/ ሌላ ተመሣሣይ ዜማ ለቋል፤ በግጥሙ ላይ መጠነኛ ማሻሻያ በማድረግ፡፡ ከባለፈው ነጠላ ዜማ የሚለየው ቢኖር ቢቢሲ የአገሬን ተቃዋሚ ፓርቲ አመራሮችን በአጃቢነት መጠቀሙ ብቻ ነው። ዋንኞቹ አቀንቃኞች ፕሮፌሰር መሥፍን ወልደማርያም፣ ፕሮፌሰር በየነ ጴጥሮስ እና ፕሮፌሰር መረራ ጉዲና ነበሩ፡፡ (እዚህ ላይ የኢትዮጵያን አይዶል ባለሙያዎችን አባባል ልዋስና) «አልተሳካላችሁም» ብላችሁስ?

ሦስቱም በአንድ አዕምሮ አስበው በአንድ አፍ እንዲህ ሲሉ ጮሁ፡፡ «የኢትዮጵያ መንግሥት በድርቅ ለተጎዱ ሰዎች እርዳታን እያከፋፈለ የሚገኘው የፖለቲካ አቋም ልዩነትን መሠረት በማድረግ ነው፡፡ ኢትዮጵያ ውስጥ እርዳታ የጭቆና መሣሪያ ሆኖ እያገለገለ ነው» በሚል፡፡

እንግዲህ ይታያችሁ። ቢቢሲ ባለፈው ዓመት «በእርዳታ ገንዘብ የጦር መሣሪያ ተሸመተበት» ብሎ ዘገበ። የእኛዎቹ ጉዶች ደግሞ ከሰሞኑ በቢቢሲ ልሣንነት ታግዘው ሰብዓዊ ዕርዳታ ለፖለቲካ መጠቀሚያነት ዋለ በሚል ማቀንቀንን ያዙ።

ውድ አንባቢዎቼ! በአፍሪካ ቀንድ ስላለው ወቅታዊ ሁኔታ ጥቂት እውነታዎችን ላስታውሳችሁ።

መላ ዓለምን ክፉኛ ያሳሰበ ረሃብና ድርቅ በአፍሪካ ቀንድ መከሰቱ ሀቅ ነው። ምናልባትም እንዲህ ዓይነቱ ክፉ ችግር በቀጣናው ሲደርስ ከ60 ዓመታት ወዲህ ይኼኛው ቀዳሚው እንደሆነ በስፋት ተነግሮለታል።

በምሥራቅ አፍሪካ 12 ሚሊዮን የሚደርሱ ሰዎች አስቸኳይ የምግብ ዕርዳታ የሚሹ ሆነው ተገኝተዋል። ዋነኞቹ የችግሩ ተጎጂዎች የኢትዮጵያ፣ የሶማሊያ፣ የኬንያና የጅቡቲ ዜጎች መሆናቸው ደግሞ ሌላው እውነታ ነው። በአሁኑ ወቅት የበለፀጉ መንግሥታትና ዓለም ዓቀፍ ለጋሽ ድርጅቶች ምንም እንኳን የተጠበቀውን ያህል ባይሆንም እርዳታቸውን እየሰጡ ነው - ይኼም እርግጥ ነው።

ከሁሉም የከፋው በሶማሊያውያን ዜጎች ላይ የደረሰው ችግር ነው፡፡ ዕርዳታ ሰጪዎች በተገቢው ተግባራቸውን እንዳያከናውኑ በዚያች አገር ያለው ወቅታዊ የፀጥታ ሁኔታ ሌላው ትልቁ እንቅፋት ሆኗል።

በመቶ ሺህዎች የሚቆጠሩ ሶማሊያውያን ቀዬያቸውን ለቀው፤ የትውልድ መንደራቸውን ትተው ወደ ጎረቤት አገራት መሰደድን ይዘዋል። ቁጥሩ እንዲህ በቀላሉ የማይገለፅ የሰው ህይወት ቀባሪ አጥቶ ከሜዳ ቀርቷል። ዕርዳታ ከሚያገኙበት ሥፍራ ሳይደርሱ ከመንገድ የቀሩ ህፃናትን ማን ይቁጠራቸው? የሚበጥሱት ቅጠልና የሚጠጡት ውኃ አጥተው በበረሃ ወድቀው የአሞራ ሲሳይ የሆኑ ከብትና እንስሳትን ማን አይቷቸው ይሆን?

ሶማሊያውያኑ በአንድ በኩል የጥይት ድምፅ እረፍት ሲነሳቸው፤ እሱም ሳያንስ የሚቀምሱትና የሚልሱት ጠፍቷቸው ጠኔው ሲጠብሳቸው፤ ሰማይ በላያቸው ላይ የተደፋባቸው ያህል ሲሰማቸው፤ ሽሽትን፣ ስደትን፣ ወደ ጎረቤት አገራት መርጠዋል። እንዲህ ያለውን ሰቆቃ «ረሀብ» ብለን ብንገልፀው እንዴት በተገባን።

አቅሙን አግኝተው፣ በለስ ቀንቷቸው የኢትዮጵያን ምድር የረገጡ ሶማሊያውያን በተዘጋጀላቸው የመጠለያ ጣቢያዎች ሆነው አስቸኳይ የምግብና የህክምና ዕርዳታ እየተሰጣቸው ይገኛሉ። በቅርቡ ለሥራ ጉዳይ የኢትዮጵያ፣ ኬንያና ሶማሊያ ድንበር መጋጠሚያ ወደሆነችው ዶሎ አዶ በመሄድ አጠቃላይ ሁኔታውን ቃኝቶ የተመለሰው ጋዜጠኛ ወዳጄ ያወጋኝም ይህንኑ ነው።

ውድ አንባቢዎቼ! ስለቁራዎች ባዶ ጩኸት ወደ ኋላ ላይ እመለስበታለሁ ማለቴን ዘንግቼው አይደለምና እነሆ:-

በመላው ዓለም እንደሚያጋጥመው ሁሉ በኢትዮጵያም በተከሰተው የአየር ለውጥ መዛባት ምክንያት 4 ነጥብ 5 ሚሊዮን የሚደርስ ህዝብ ዕርዳታ ፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል።

የአገሬ ተቃዋሚዎች አዘውትረው የሚጠቀሙበትን ቃል ተውሼ አሁን በኢትዮጵያ የተከሰተው ችግር «ድርቅ» ሳይሆን «ረሀብ» ወይም «ጠኔ» ተብሎ ሊገለፅ ይችላል ብዬ አፌን ሞልቼ ለመናገር ድፍረቱን አጣለሁ - ከፍተኛ የሆነ መሠረታዊ የትርጉም ልዩነት አለውና።

ብቻ የፖለቲካ ትርፍ ለመሸመት ሲባል የተዛባ ትርጓሜ በመስጠት የአገርን መልካም ገፅታ ማጨለምና በጎ ሥዕልን ማጥቆር ህሊና ላለው ሰው ምን ሊባል ይችላል - ክፉ አሳቢ ወይንስ ሟርተኛ?

ድርቁ ባስከተለው ችግር ለምግብ እጥረት ለተጋለጡ ዜጎቻችን መንግሥታትና ለጋሽ ድርጅቶች ቃል የገቡትን ዕርዳታ እስኪያቀርቡ ድረስ የኢትዮጵያ መንግሥት ለአስቸኳይ ጊዜ በመጠባበቂያነት ከያዘው ክምችት ውስጥ አውጥቶ እያከፋፈለ ይገኛል - በጎ ተግባር።

ድርቁ ባስከተለው ችግር በተፈጠረው የምግብ እጥረት ምክንያት ህይወቱ የተቀጠፈ፣ ከመኖሪያ ቀዬው ወደ ሌላ ክልል የተፈናቀለ፣ መንደሩን ለቅቆና ድንበር ተሻግሮ ወደ ጎረቤት አገራት የተሰደደ ዜጋ በዛሬይቱ ኢትዮጵያ እንደሌለ ብዙዎች ምስክርነታቸውን የሰጡት ጉዳይ ነውና ይኼን በዚሁ ልለፈው።

ኢትዮጵያ ከፍተኛ የምጣኔ ሀብት ዕድገት እያስመዘገቡ ካሉ ጥቂት የአፍሪካ አገሮች አንዷ እንደሆነች፤ መግሥትም በሚከተለው ፖሊሲ አገሪቱ በትክክለኛው የዕድገት ትራክ ላይ መሆኗን እንደሚያሳይ በቅርቡ የአሜሪካ የውጪ ጉዳይ ሚኒስትር ሒላሪ ክሊንተን ማረጋገጣቸው በአገሬ ተቃዋሚ የፖለቲካ አመራሮች ዘንድ ይህ እውነታ ምን ትርጓሜ ተሰጥቶት ይሆን?

የዓለም የምግብ ፕሮግራም ዋና ዳይሬክተር በበኩላቸው ኢትዮጵያ ለግብርናው ዘርፍ ልዩ ትኩረት ሰጥታ እየሰራች መሆኗ የዜጎቿን የምግብ ዋስትና በአጭር ጊዜ ውስጥ ለማረጋገጥ ያስችላታል ማለታቸውስ እንዴት ታይቶ ይሆን?

የተቃዋሚ መሪዎች ይህን መልካም ተግባር ማሞካሸት ባይጠበቅባቸውም ጠንካራ ጎኖች ይበልጥ የሚጎለብቱበትን፤ ደካማ አሰራሮች ካሉም የሚታረሙበትን አቅጣጫ በመጠቆም ለአገር ዕድገት በጐውን ማሰብ ብሎም ለህዝብ ኑሮ መሻሻል ቀናውን መመኘት ቢችሉ እንዴት ጤናማ በሆነ፡፡

መንግሥት በዕርዳታ እህል አከፋፈሉ ሥርዓት ላይ ልዩነትን ይፈጥራል፤ ዕርዳታን ለፖለቲካ መሣሪያነት ይጠቀምበታል ብሎ መኰነን የጤና ይሆን? እናም የየኤምባሲዎችን ደጅ እየጠኑ ዕርዳታ አትስጡ፣ አታብሉና አታጠጡ ብሎ ዘመቻ ማካሄድ በየት ዓለም ያለ ፈሊጥ ይሆን?

ድንበር አቋርጠው ወደ ግዛቱ የገቡ የጐረቤት አገር ዜጐችን እጆቹን ዘርግቶ በመልካም ሁኔታ ተቀብሎ እያስተናገደ የሚገኝ መንግሥት በራሱ ወገን ላይ እንዲህ ዓይነት ጭካኔ፤ ይህን መሰሉን አድሏዊ ተግባር ይፈፅማል ተብሎ እንዴት ይታመናል፡፡

ምኞታቸው አይስመር፣ ፍላጐታቸው አይሳካ፣ ውጥናቸው አይስራ፣ ህልማቸው አይፈታ እንጂ እንደ እነሱ…እነሱማ ዜጐች ክፉኛ በሰቆቃ ተሸብበው በህይወትና ሞት መሃል በተገኙ ነበር፡፡

የዓለም ተሞክሮዎች እንደሚያሳዩን በአንድ አገር ሰው ሰራሽ ሆነ ያልተጠበቁ የተፈጥሮ አደጋዎች ሲያጋጥሙ አሊያም በዚያች አገር ወረራ ተካሂዶ ሉዓላዊነቷ ሲደፈርስና ነፃነቷ ጥያቄ ውስጥ ሲወድቅ በልዩነት ጐራ ቆመው የነበሩ የፖለቲካ ፓርቲዎች መላ ህዝባቸውን በአንድነት አስተባብረው ይቆማሉ፤ ሐብትና እውቀታቸውን በጋራ አቀናጅተው ይሰራሉ፡፡ በዚህም ዜጐቻቸውን ከተጋረጡባቸው አደጋዎች ይታደጓቸዋል፤ የተፈፀመባቸውንም ወረራ በፅናት ታግለው ይቀለብሱታል፡፡

ከዚያም በኋላ ወደቀድሞው ልዩነቶቻቸው ተመልሰው ሠላማዊ የፖለቲካ ትግላቸውን በየጐሬያቸው ሆነው ይቀጥላሉ፡፡ በሥልጣን ላይ ያለን መንግሥት በኃይል ለመጣል የሚታገሉ ቡድኖች እንኳን ሳይቀሩ በዚህ ወቅት አገሯዊው ችግር እስኪቃለል ነፍጣቸውን አኑረው ለገዥው ፓርቲ ፋታ እንደሚሰጡት የብዙዎች አገሮች አማፅያን የትግል ልምድ ያስተምረናል፡፡

ይህ በአብዛኛዎቹ አገሮች ሲሰራበት የቆየ ወደፊትም ይበልጡን ጐልብት የሚቀጥል ሥልጡን አካሄድ እንደሆነ የሚታመን ነው፡፡ የሚያሳዝን ሆኖ ይህን አሰራር ከእኛዎቹ ፖለቲከኞች ዘንድ ለማየት አልታደልንም - መቼም ከሌላ ፕላኔት የመጡ ናቸው ካልተባለ በስተቀር፡፡

እንደ እነሱ ፍላጐት ቢሆን ኖሮማ በችግር ላይ ያሉ ዜጐች እስትንፋሳቸው ሳይቋረጥ ዘለው ጉሮሮአቸውን ሊያንቁ፤ በቅርብ ርቀት ተጠባብቀው ዓይኖቻቸውን ቧጥጠው ሊያወጡ እንደቋመጡ ቁራዎች አድፍጠው በተቀመጡ ነበር፡፡ ሰዎች በጠኔ ተመትተዋል፤ በረሃብ ቸነፈር ተገርፈዋል እያሉ መዓት ያወርዳሉ፡፡ ቁራዎቹም ይጮኃሉ፤ ቢቢሲም ይህንኑ ተቀብሎ ያስተጋባል፡፡

መላው የኢትዮጵያ ህዝብ ለዘመናት አብሮት የኖረውን ድህነት ከላዩ ላይ እስከ ወዲያኛው ለመጣል ቃል ኪዳኑን በህብረት ያደሰበት፤ አገራዊውን የአምስት ዓመት የዕድገትና የለውጥ ዕቅድ ገቢራዊ ለማድረግ የመጀመሪያውን መንደርደሪያ ዓመት በስኬት ባጠናቀቀበት፣ ከብልፅግናው ማማ መወጣጣት እንደሚቻል ብሩህ ተስፋ ባየበት ዋዜማ የቢቢሲ ሰሞንኛ ዶክመንተሪ ዘገባ ይፋ መሆንን አንባቢዎቼ ልብ ብለውት እንደሚሆን እገምታለሁ፡፡

ቢቢሲ ምን ጣጣ አለበት - ዓመት ቆይቶም ቢሆን በተዛባው መረጃው ተፀፅቻለሁ በቅጥፈት ለተሞላው ሰሞነኛው ዶክመንተሪ ዘገባውም በተለመደው አቀራረቡ የዳግም ይቅርታ መጠየቂያ ሪፖርት ስላለማውጣቱ እንዴት እርግጠኛ መሆን ይቻላል፡፡

በምንም መመዘኛ ተሳስቻለሁና ይቅርታ እጠይቃለሁ ማለት ጨዋነት የተመላበት አቀራረብ ነውና ይከበራል፤ ትልቅ ዋጋም ያሰጠዋል፡፡ ስህተትን አምኖና ጥፋትን ተቀብሎ ይቅርታ መጠየቅ ዘመናዊነት እንዲያም ሲል ሥልጡንነት ነውና፡፡

“በረሃብ ሰቆቃ ላይ ከሚገኝ ዜጋ ጉሮሮ ተነጥቆ የጦር መሣሪያ ተሸመተ፤ ለድርቅ ተጐጂዎች እርዳታ የሚከፋፈለው በፖለቲካ ወገንተኝነት እየተለየ ነው” ብሎ በጭፍን መዘገብ ግን ተዓማኒነትን ያሳጣል፤ የሰብዓዊና የሞራል ጥያቄንም ያጭራል፡፡

ግና እውነታው ይህ አልነበረም፡፡ ህወሓት ያኔ እንዲያ ዓይነቱን አሳዛኝ ድርጊት ፈፅሞ ቢሆን ኖሮማ ከቶ እንዴት ለዛሬው ድሉ ሊበቃ በቻለ ነበር፡፡

ግና እውነታው ይህ አልነበረም፡፡ ህወሓት ያኔ ለዘመናት ማንነቱ ተረስቶ፣ ዴሞክራሲያዊና ሰብዓዊ መብቶቹ ተረግጠው፣ በግፍ ቀንበር ሥር ሲማቅቅ የኖረን አርሶ አደር ሰቆቃ ተጋርቶ የነፃነት ችቦን የለኮሰ፣ የጭቁኖች ድምጽ ሆኖ ከጨለማ ወደ ብርሃን ያሸጋገረ የህዝብ ልጅ ነውና ወዳጅ በፍቅር ይቀበለዋል - ቁራዎች ቢጎመዝዛችሁም፡፡

ሁሉንም አቅጣጫዎች ፈትሾ፣ ላይ ታቹን፣ ግራ ቀኙን መዝኖ፤ ሀቁን ከሀሰት ለይቶ፤ ምሉዕ መረጃዎችን ሰባስቦና የወሬ ምንጮችን ተዓማኒነት አጣርቶ፤ ሚዛናዊነትን በጠበቀ ሁኔታ ለሚቀርብ ዘገባ ዘወትር ታላቅ አክብሮት አለኝ፡፡ መሠረተ ቢስ፣ ያልተጨበጠና ያልተረጋገጠ ወሬን ሰንቆ ማናፈስ ግና ትዝብት ላይ ይጥላል፡፡

የሆነ ሆኖ ቢቢሲ ኳሲቷን ይለጋታል - ሒዩማን  ራይትስ ዎች ይቀበላል፣ ሦስቱ ቁራዎችም አፋፍሰዋት ይጮኃሉ፡፡ መልሰው ቁራዎቹ ያላዝናሉ፣ ሒዩማን ራይትስ ዎችም ተቀብሎ እሪታውን ያቀልጠዋል፣ ቢቢሲም ይህንኑ ያራግባል፡፡ ሁሉም እየተቀባበሉ ይጫወታሉ፤ ይንጫጫሉ፤ ይጯጯኃሉ፡፡ የመጨረሻው ድምር ውጤታቸው ግን በአየር ላይ ያለን ጉም መዝገን ብቻ ይሆናል -  ሠላም፡፡